# እውነት ትግራይ መሬት ቆርሳ ወስዳለችን ?

## ሀቅ ለፈለገ ሀቁ ይህ ነው

(Part — Two) Hidase-Ethiopia

## የትግራይ ክልል መሬት ወወሰደ.ል ወይስ ተወሰደ.ል

ዘውዳዊው ስርዓት በህዝቦች ዓመፅ ከስልጣን ሲወገድ ወደ ስልጣን የመጣው ወታደራዊው የደርግ መንግስት ሁሉም የዴሞክራሲ መብቶች በአዋጅ በማፈኑ በርካታ የህዝብ ጥያቄ ያነገቡ ድርጅቶች ለትጥቅ ትግል በረሀ ገብተው ነበር፡፡ የአብዛኛው ድርጅቶች ጥያቄ አንድ የሚያደርጋቸው ብሄራዊ ጭቆና የሚል ነበር፡ ፡ ደርግ ተደምስሶ ኢህአዴግ ስልጣን ሲይዝ የነበሩ የማንነት ጥያቄዎች በሙሉ መልስ ለማግኘት ችለዋል፡፡

በዚህ ጊዜ ነበር የህገመንግስት ማርቀቅ ጉዳይ ሲጀመር የአካለል ጉዳይ በብሄር ብሄረሰብ ቋንቋ፣ ባህል እና አኗኗር ዘይበ መሰረት መሆን እንዳለበት ሲደነገግ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰብ እና ህዝቦች በዝርዝር ተወያይተውበት ወደየ ፍላጎታቸው እንዲካለሉ ተደርጓል፡፡ ለምሳሌ የትግራይ ብሄር ተወላጆች ባለፉት ስርዓታት ወደ ጎንደር እና ወደ ወሎ ተካልለው የነበሩ ወደ ትግራይ እንዲካለሉ ተደርጓል፡፡ የሌሎች ብሄር ብሄረሰብ እና ህዝቦችም እንደዛው በየ ቋንቋቸው እንዲካለሉ ተደርጓል፡፡

እዚህ ላይ የትግራይ አከላለል ስናይ ከድሮ ጀምሮ ትግራይ የሚባል በጎንደር እስከ እምባ ጊወርግስ የሚዘልቅ ሲሆን በወሎ ደግሞ እስከ አይሎሃ ወንዝ በተለምዶ



ህዳሴ ኢትዮጵያ hidaseethiopia@yahoo.com ወይም hidaseethiopiaa@gmail.com

አይሎሃ ምላሽ የሚል ስያሜ የተሰጠው እስከ ወልድያ ዶሮ ግብር አከባቢ ያለውን የአይሎሀ ወንዝ ማለት ነው፡፡

ይሁን እና በዚህ አከባቢ በደንብ ለመለየት እስከሚያስቸግር ድረስ የሁለቱም ብሄሮች ማለትም የአማራ እና የትግራይ ተወላጆች ስላሉ ***በታሪክ ብቻ መሰረት በማድረግ ከማካለል ግጭቶች እና የይገባኛል ጥያቄዎችን ለመቸነስ ህዝቡ በራሱ ፈቃድ ይለይ ተብሎ የትግራይ ክልል በጎንደር ከእምባ-ጊወርግስ መሆኑ ቀርቶ እስከ ፀለምቲ፣ በወሎ ደግሞ እስከ ከአይሎሀ ምላሽ መሆኑ ቀርቶ አሁን ካለበት ዋጃ ምላሽ ተደረገ፡፡*** ይህ አካለል በሁለቱም ህዝቦች ስምምነት ላይ ተደርሶ ባለፉት 27 ዓመታት ምንም ችግር ሳይደርስ ቆይቷል፡፡

የትግራይ ክልል አሁን የምናየው ቅርፅ የያዘው ታሪካዊ አመጣጥ ስላለበት ወይም ከአሁን በፊት እያስተዳደረው ስለነበር በሚል እሳቤ አይደለም፡፡ የትግራይ የግዛት አስተዳደር ይሁን የሌሎች ሁሉም 9 ክልሎች ያላቸው የግዛት ወሰን በአዲሱ አመለካከት ወይም በህገመንግስቱ መሰረት ብሄርን መሰረት ያደረገ አካለል ነው፡፡ ***ትምክህተኞች እያነሱት ያለው ጥያቄ የተምታታ ነው፡፡*** ትምክህተኞች አማራ የሚባል ብሄር የለም ሲሉ የነበረ፣ አንድ ኢትዮጵያ ናት ያለችው ሲሉ የነበረ ሲሆን፤ አሁን ደግሞ በኢህአዴግ አመለካከት ገብተው ወልቃይት የኛ፣ ራያ የኛ ሲሉ ይደመጣሉ፡፡

***እንደ ትምክህተኞች ጥያቄ ይጠየቅ ከተባለ - ትግራይ ሊጠይቅ ከሆነ ከእምባ ጊወርግስ እስከ አይሎሀ ምላሽ ነው፡፡ ነገር ግን የትግራይ ህዝብ ይህ አልጠየቀም፡፡*** ሰፊ መሬት ስላልፈለገ አይደለም፡፡ የትግራይ ህዝብ ለብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች መብት መከበር ሲል 60 ሺ ሰማእታት እና ከ100 ሺ የአካል መጉደል መስዋእትነት ከፍለዋል፤ በዚህ ብቻም አልቆመም ከ62 ሺ ስኴር ኪ.ሜ. ቦታውም ለህገመንግስቱና ለህዝቦች መብት መከበር ሲል ወደሌላ ክልል እንዲካለሉ ፈቅዷል (ከ114 ሺ ስኴር ኪ.ሜ. የአስተዳደር ወሰን ወደ 53 ሺ ስኴር ኪ.ሜ. ወሰን ነው

የያዘው)፡፡ ይህ ሁሉ መስዋእትነት ሲከፍል ሞኝነት ወይም የዋህነት አይደለም፡፡ ***አንዲት እና ጠንካራ አገር፣ የሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች እኩልነት ያስከበረች አገር፣ ከመገንባት አንፃር ያለው ፋይዳ በመረዳት ነው፡፡*** የትግራይ ህዝብ ይሁን ህወሓት አንድን ጠንካራ አገር ከመፍጠር አኳያ የማይሸራረፍ ጠንካራ አቋም ያላቸው መሆኑ ማሳያ ነው፡፡




*ስዕል 1 በህገመንግስቱ መሰረት ወደ ሌላ ክልል የተካለለ የትግራይ ታሪካዊ ወሰን*

የነፍጠኛው ቡድን አሁን እየጠየቀ ያለው የግዛት ይገባኛል ጥያቄ መሰረተ ቢስ ከሚያደርጉት ምክንያቶች አንዱ፣ በዘመነ ሚኒሊክ ይሁን በዘመነ ሀ/ስላሴ ትግራይ የሚባል ግዛት እንጂ አማራ፣ ኦሮሞ፣ አፋር፣ ሶማሌ፣ ቤንሻንጉል፣ ጋምቤላ፣ ደቡብ ህዝቦች፣ ሀረሪ የሚባሉ ግዛቶች አልነበሩም፡፡ ***ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ማንነታቸው ሲታፈን፣ ሲዋረድ እና ሲንቋሸሽ፣ የማንነት ጥያቄ ሲጠይቁም***

## መጤዎች ናቹ፣ ሰደተኞች ናቹ አርፋቹ ተቀመጡ የሚል ምላሽ ነበር የሚሰጣቸው፡፡

እነዚህ 9 የአስተዳደር ክልሎች በስራቸው ያሉ ህዝቦች ማንነታቸው እውቅና አግኝቶ ራሳቸው በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ ዕድል ያገኙት ለመጀመሪያ ጊዜ በኢህአዴግ ነው፡፡ ታድያ

- የአማራው ትምክህተኛ ቡድን ኬት ያመጣው ነው ወልቃይት እና ራያ የአማራ ነው የሚለው ?
- አማራ የሚባል ብሄር የለም ሲል አልነበረም እንዴ? ወልቃይት የጎንደር ራያ የወሎ ማለት አይቀለውም ነበር?
- በዘውዳዊ ስርዓት ይሁን በደርግ ጊዜ አፋር የሚባል አስተዳደራዊ አካለል ነበር እንዴ?
- በዘውዳዊ ስርዓት ይሁን በደርግ ጊዜ ኦሮሞ የሚባል አስተዳደራዊ አካለል ነበር እንዴ?
- በዎሎ ስር ይተዳደር የነበረ ሰፊ መሬት እንደ ራያና ወልቃይት ወደ ሌላ ክልል /አፋር/ እንዲካለል አልተደረገም እንዴ? በወሎ ሲተዳደር የነበረ ልዩ የኦሮሞ ዞን አልተባለም እንዴ?
- በሸዋ ክፍለ-ሀገር ስር ሲተዳደር የነበረ ሰፊ ቦታ አሁን ልክ እንደ ወልቃይት እና ራያ የተደረገው ዓይነት፣ የኦሮሞ ብሄር በመሆናቸው ወደ ኦሮምያ አልተካለሉም እንዴ?
- ኦሮሞ ብሄር እንደ ትግራይ የራሱ አስተዳደር አላቋቋመም እንዴ?
- በጎጃም ሲተዳደር የነበረ ቤንሻንጉል ብሎ አላወጀም እንዴ? ወዘተ
- ታድያ የአማራው ትምክህት እንዴት አሁን በትግራይ ጣቱን ይቀስራል? ራሱ ትምክህተኛ ይመልሰው፡፡



ህዳሴ ኢትዮጵያ hidaseethiopia@yahoo.com ወይም hidaseethiopiaa@gmail.com

በአጠቃላይ የትምክህተኛው ሀይል እያነሳው ያለ ጥያቄ፣ የኢትዮጵያን አንድነት ስጋት ውስጥ ስለገባ ወይም ለኢትዮጵያ አንድነት ስለተቆረቆረ ሳይሆን፣ አገራችን ኢትዮጵያ ወደ ኋላ ወደ 19ኛው ክ/ዘ በመመለስ እርስ በራሳችን ለማተራመስና ወደ ማያቧራ ግጭት ለማስገባት እንጂ ሌላ ምንም እርባና የለውም፡፡

# ማጠቃለያ

በአጠቃላይ የትግራይ ህዝብ ለማንነቱ እና ለመብቱ ሲታገል የህዝቦችን መብት ለመንካት ሳይሆን የሌሎች ህዝቦች መብትም ልክ እንደ ራሱ መብት ለማክበር በመሆኑ እላይ ስዕል ላይ እንደሚታየው ስፋቱ 62.2 ሺ ስኴር ኪ.ሜ. የሆነ፤ 2092 ኪሎሜትር ዙርያ ያለው የመሬት ወሰን፣ ምንም እንኳ በታሪካዊ አመጣጥ የትግራይ ቢሆንም፤ በታገለለት ዓላማ መሰረት በመርሆ /የአፋር እና የአገው ብሄር አካለል/ እንዲሁም በህዝብ ፍላጎት /ከእምባ ጊወርግስ እስከ አይሎሃ ምላሽ ያለው አካለል/ ወደ ሌላ ክልል እንዲካለል አድርጓል፡፡

ነፍጠኞች እና ትምክህተኞች እንደሚሉት ህወሓት ትግል ሲጀመር የትግራይ ሪፓብሊክ ለመመስረት እንደሆነ ነገር ግን ለጊዜው አቁሞ ጊዜ በመውሰድ ላይ ነው ያለው የሚል ወሬ መሰረት የሌለው ለፖለቲካ ትርፍ ተብሎ የተፈበረከ ነው፡
፡

በእርግጥ ህወሓት በረሀ ሲወጣና ትግል ሲጀምር የትግራይ ካርታ ብሎ የተነሳው በታሪካዊ አመጣጡ እላይ ያየነው ስዕል ማለትም በዎሎ አይሎሃ ምላሽ እና የተወሰኑ የአገው ምድር፣ በጎንደር ወልቃይት ብቻ ሳይሆን በታሪክ የምናውቀው እስከ እምባ-ጊወርግስ በአፋር ደግሞ እስከ ኤርትራ ድንበር የሚዘልቅ ነበር፡፡ በዚህ አከባቢ ያሉ ህዝቦች ሁሉም /ትግራዋይ፣ አፋር፣ ኢሮብ፣ ኩናማ እና አገው/ በህወሓት ስር ተደራጅቶ ታግሏል፡፡ ይህ ትግል ሲደረግ ግን የትግራይ ነፃ መንግስት ለመመስረት አልነበረም፡፡ ቢሆን እማ ደርግን በመደምሰሱ ማንም የሚከለክል ሀይል አልነበረም፡፡



ህዳሴ ኢትዮጵያ hidaseethiopia@yahoo.com ወይም hidaseethiopiaa@gmail.com

ደርግ ከመደምሰሱ በፊት የኢትዮጵያ ግዛት ኤርትራን ያካተተ ነበር፡፡ ነገር ግን የኤርትራ ህዝብ ነፃነት ይፈልግ ስለነበር 30 ዓመት ነፃነትን ያነገበ ከፍተኛ መስዋእትነት በመክፈሉ እነሆ ነፃነቱን አስከብሯል፡፡

የትግራይ ህዝብ ሲታገል የትግራይ ነፃ መንግስት ሊመሰርት ቢሆን ኑሮ ማንም አይዘውም ነበር፡፡ በዛን ጊዜ በአገራችን ኢትዮጵያ ከ17 በላይ የታጠቁና የተደራጁ የፖለቲካ ፓርቲዎች የነበሩ ቢሆንም ከፍተኛ ሀይል የነበረው በጠቅላላው በኢትዮጵያ ከነበረው የታጠቀ ሀይል ከ95% የህወሓት ወይም የትግራይ ህዝቦች ሰራዊት ነበር፡፡ *በመሆኑም የትግራይ ነፃ መንግስት የመመስረት ህልም ቢኖር ኢትዮጵያ የምትባል አሁን አናያትም ነበር የተበታተነች እርስ በርሷ የምትናከስ ሁለተኛ ሶማሊያ ትኖር ነበር እንጂ፡፡ በዛን ጊዜ የትግራይን ፍላጎት ወደ ኋላ የሚመልስ ሀይል ከቶም አልነበረም፡፡*

ነገር ግን የትግራይ ህዝብም ህወሓትም አንድ ጠንካራ ዴሞክራሲያዊት እና በህዝቦች ፍላጎት እና ይሁንታ የሚመራ ስርዓት ያላት ታላቅ አገር መመስረት የሚል ዓላማ በመሆኑ ለዚህ ዓላማ መሳካት የትግራይ ህዝብ ከፍተኛ መስዋእትነት ከፍሏል፡፡ *እነሆም ከወንድም ህዝቦች በመሆን ታላቅ አዲስቷ ኢትዮጵያ መስርተን እንገኛለን፡፡ ምንም እንኳ ነፍጠኞች እና ትምክህተኞች የኢትዮጵያ የ3ሺ ዘመን ታሪክ የራሳቸው ብቻ አድርገው ሲፅፉት እና ሲያወድሱ ቢታይም የትግራይ ህዝብ ግን የ3000 ዘመን ታሪክ ተካፋይ እና ዋና ተዋናይ የነበረ፣ በዚህ ታሪክም የሚኮራ በመሆኑ ነፃ መንግስት ለመመስረት አልሮጠም፡፡*

ህወሓት እና የትግራይ ህዝብ

- የትምክህት አራማጅ ገዢዎች እና ሰፊው ህዝብ ለይተው ስለሚያዩ፣
- የኢትዮጵያ ህዝቦች ተባብረው ዴሞክራሲያዊ አንድነት ያለው ህዝባዊ መንግስት ከመሰረቱ ኢትዮጵያ እንደ ታሪኳ ወደ ገናናነትዋ ትመለሳለች ብለው ስለሚያምኑ ነው ከፍተኛ መስዋእትነት የከፈሉት፡፡



ህዳሴ ኢትዮጵያ *hidaseethiopia@yahoo.com* ወይም *hidaseethiopiaa@gmail.com*

ታድያ ህወሓት ይህን ትቶ እንዴት ይሄዳል? ወዴት ይሄዳል? ነፍጠኞች በራሳቸው ይመልሱት፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ የትግራይ ህዝብ ታግሎ ያረጋገጠው ማንነት ዳግም ወደኋላ ለመመለስ፣ ማንነቱ ለማዋረድ፣ የሚደረግ ጥረት ካለ ግን ቆሞ አያይም፡፡ ይህን በከፍተኛ መስዋእትነት የተረጋገጠ መብት ረግጦ ወደ ትምክህት የሚመልስ ሀይል ካለ ግን ፈፅሞ አይቀበልም፡፡ ከተቻለ ከመላ የአገራችን ህዝቦች በመሆን ይታገላል ካልሆነም እንዳለፈው በትግሉ መብቱን ያስከብራል እንጂ፡፡

**ህዳሴ ኢትዮጵያ**

**ሕዳር 16፣ 2011 ዓ.ም.**

*hidaseethiopia@yahoo.com* ወይም *hidaseethiopiaa@gmail.com*